# “የዲባቶ መስፍን አረጋ ስራ፣ ከልሳንሲንም (Linguistics) በላይ ነው”

ፍስሃ ‘ተማሪ’ መሆኑንና “… ዞሮ ዞሮ አስፈላጊው ማእረጌ ሳይሆን ስራየ ነው…” ብሎን ሲያበቃ፣ “..ስራውን ልንገመግም የሚያስችለንን… መለኪያ… ከውጥን ጽሁፉ..” ውስጥ መዞ ያውጣውን አንቀጽ አስፍሮልናል። ይህ ያሰፈረው ጽሁፍና፣ የዲባቶ መስፍን የልሳንሲን [1] (Linguistics) ስራ፣ በዙሪያ ጥምጥም ካልሆነ በስተቀር፣ ጨርሶ አለመገናኘቱ ብቻ ሳይሆን፣ በቁጥር 2 ግርጌ ማስታውሻ የጠቀሳቸው ፕሮፌሰር ጌታቸው ሃይሌ፣ በቁጥር 4 እና 6 ግርጌ ማስታውሻዎች የጠቀሳቸው ሌሎች ቱባ ቱባ ምሁራን ሁሉ የሰሯቸው ስራዎች (አንባቢ እንዲፈርድ ከተጠቀሱት ምሁራን ካንዱ ጋር የተደረገ ቃለ-መጠይቅ፣ የተቀነጨበ አስተያየት እና የጻፏቸውን መጽሃፍት የየምእራፉ ርእስ *[ርእስ ብቻውን የተሟላ መረጃ ሊሰጥ ባይችልም፣ እዚህ [2] መመልከት ይቻላል]* በተዘዋዋሪ እንደሆነ እንጂ፣ በቀጥታ ስለ ልሳንሲን የጻፉት ሃሳብ ያለ አይመስልም።

ተማሪ ፍስሃ (ግርጌ ማስታወሻ 6 ላይ)፣ *“የጥንቱን የመሰረቱን ጥሎ፣ የዛሬውን የቆጡን የባጡን ብቻ አንጠንጥሎ የተደረገው ጉዞ፣ የቱን ያህል እንደጎዳን በመገንዘብ ‘ሚጠት’ (Return/Homecoming/Restoration) ያሻናል የሚሉ ብቻ ሳይሆኑ ለዚሁ አስፈላጊ የመሰላቸውን ያይምሮ ስንቅ እያዘጋጁ ያሉ መሆናቸውን ተረድቻለሁ። የነዚህ ምሁራን ስራ በርግጥ ተስፋ ፈንጥቆልኛል…”* [3] ይለናል።

---

[1] ለ‘linguistics’ ‘ስነ-ልሳን’ (የተለመደው ጥምር-ቃል) ስላለ፣ መስፍን ለምን ‘ልሳንሲን’ እንዳለው ገርሞኝ ተመልሼ አየሁ። በዚሁ ሙያ ውስጥ ያለውን ሰው ‘linguist’ቱን ባማረኛ ማን ነበር የምንለው? ‘የስነ-ልሳን ባለሙያ?’ የስነ-ልሳን አጥኚ? ‘የስነ-ልሳን ተመራማሪ? የስነ-ልሳን ምሁር?። ‘chemistry, physics, anthropology, biology …’ ለመሳሰሉትስ የት/ሙያ መስኮች ሁሉ አማረኛ አላቸው? በየሙያዎቹ ያሉትንስ ሰዎች ማን አልናቸው? ለመስኩ/ጥናት ዘርፉ (ኬሚስትሪ, ፊዚክስ… ወዘተ የሚለውን) እንዳለ እንግሊዝኛውን እንጠቀም እንበል፣ ባለሙያዎቹንስ? ለbiology “ስነ-ህይወት” እንዳለው አውቃለሁ። biologist ቱን ማን እንበለው? የስነ-ህይወት አጥኚ? የስነ-ህይወት ባለሙያ? የስነ-ህይወት ተመራማሪ? አንብቢዩ ጸሃፊም ይሁኑ አንባቢ፣ ወይም ሁለቱንም፣ እስቲ ካሁን ቀደም እነዚህን የባለሙያዎች ስሞች ማን ብለው እንደጻፉ/እንዳነበቡ አንድ ጊዜ ያስቡት! ስንት ዝብርቅርቅና ውጥንቅት ነው ያለው? ህግና ስርአት የወጣለት አንድ ቃል አለን? እንግሊዝኛው ‘_ist’ “_er” “_or”ን (suffix) እያስከተለ linguist፣ chemist, physicist/cian, anthropologist, biologist auto/biographer እንደሚለው ሁሉ, ላማረኛም ‘-ኛ’፣ “_ሲነኛ”ን እና/ወይም ‘_ፈናኝ’ን የመሳሰሉትን ኋልጡፎች (suffixes) ነው የፈጠረልን። ‘ስነ-ልሳን’ ን በ‘ልሳንሲን’ የቀየረውም ‘ልሳንሲነ-ኛ’ እያለ “የሚረባ/ኋልጡፉን የሚቀበል” ቃል ስለሆነ ነው። ‘ስነ-ልሳን’ አይረባም። የአማረኛው ፊልጡፍ (prefix) “ስነ” የንግሊዘኛው ‘suffix’ “_logy” እኩያ ይመስለኛል። በመሆኑም ‘ልሳንሲነ-ኛ’ ሲል “ስለ ልሳን የሚያጠና፣ የሚመራመር..ወዘተ ማለት ይመስለኛል። “scientist”ን “ሰገለ_ኛ” ያለው ከላይ ከጠቀስኳቸው ምስቅልቅሎች የሚያውጡንን እነዚያን ኋልጡፎች ስለፈጠረ ነው።

ይህን ሰው ‘እሰይ’ ‘አበጀህ’ ማለት ይቅር፤ ‘ቀድረ-ቀላል’፤ “..እንደነ ስም አይጠሩ… አገኝ አጣውን አግበስብሶ በላያችን ላይ የሚያፈስሱብን..” ሊባል ይገባዋል?። ይህ ሙያዊ ሂስ/ትችት ነወ? ሰይጣንን እንደሚጠራ ደብተራ ለምንስ “..እንደነ ስም አይጠሩ…” ማለት አስፈለገ? ሰውየው በግልጽና ባደባባይ ሰሙን ከነ መኖሪያው ነገረን አይደል?

[2] http://www.store.tsehaipublishers.com/product_print.php?products_id=102

http://www.senamirmir.org/theme/5-2001/gh/cup.html (ፕሮፌሰር ጌታቸው ሀይሌ ቃለ መጠይቅ)

[3] http://www.quatero.net/pdf/fisiha-on-dibato-26aug.pdf

እነዚህ ምሁራን በአማርኛ ልሳንሲን አካባቢ ብቻ ሳይሆን፣ ዲባቶ መስፍን እየሰራ ባለው ስራ አካባቢ ካሁን ቀደም የትኛው መጽሃፍና ገጽ ላይ ምን ጽፈዋል? ዲባቶ መስፍን በሰራበት የልሳንሲን ሙያ አካባቢስ "..የፈነጠቁልህ ተስፋ..." ምንድን ነው? ተማሪ ፍስሃ፣ አንተ ያልከውንስ እንዴት ይደግፋሉ? የትኛው ገጽ ላይ? ምሁራዊ/ሙያዊ አስተያየት መሆን ያለበት እንዲህ ይመስለኛል። እነዚህ ምሁራን ከጻፏቸው ጽሁፎች ርእሶች እንደተረዳሁትና (መጽሃፉ ከተዋቀረባቸው ምእራፎች ያንዱ ደራሲ ከሆኑት ምሁር ጋር አጭር የጾዳቤ [እሜይል] ልውውጥ አድርጌያለሁ) ስለ ልሳንሲን (linguistics) አለመጻፋቸውን ነው የነገሩኝ። ተማሪ ፍስሃ፣ የነዚህን ምሁራን ስራ የሚያደንቀው በ'ሚጠት' (Return/Homecoming/Restoration) ላይ "..የፈነጠቁለት ተስፋ..." ስላለ ነው።

"አውቆ የተኛን ቢቀሰቅሱት..." ሆኖ እና እልፍም ሲል፣ ዲባቶ መስፍን እንዳለው "በሰበካ ሽወዳ" ሆኖ ነው'ንጂ፣ ተማሪ ፍስሃ የሚመኘው ስለ እውነት 'ሚጠት' (Return/Homecoming/Restoration) ከሆነ፣ የንግሊዝ ቃላት በሙሉ ባማረኛ ሲተኩልን፣ ወደ ቋንቋችን መመለስ (Return)፣ ወደ ቤተኛ ቋንቋችን መመለስ (Homecoming) አይደለምን? ግእዝንም መሰረት አድርጎ፣ ከሌሎችም አገራዊ ቋንቋዎች ቃላት መፍጠርና ወደ ኢትዮጵያዊ ብሄርነት መመለስ (Restoration) አይደለምን? ይህ ካልሆነ፣ እነዚህ የተጠቀሱት ምሁራን፣ የትኛው ገጽ ላይ ስለ አማርኛ ቋንቋ ልሳንሲን፣ (በዙሪያ ጥምጥምም እንኳን ቢሆን)፣ ምን አሉ? ጥቀስልና እስቲ አሳየን?

> "...አማረኛችን በባእድ ቋንቋዎች-በተለይም ደግሞ በንግሊዝኛና በመጠኑም ሃይማኖትን አስታኮ በአረብኛ-ክፉኛ እየተጠቃ ይገኛል። ይህ እዚህ ግባ ይባል ያልነበረው ቋንቋ-ለቋንቋው ባለቤቶች ምስጋና ይግባውና--ዛሬ ከግሪክ፣ ላቲን፣ ህንድ ወዘተ አግበስብሶ በመለቃቀም ባከማቸው ሰራዊቱ ተጠናክሮ በመምጣት....አማረኛን ሊደመስሰው ከምድረ ገጽ ሊያጠፋ--በገዛ ቤቱ ውስጥ ጓዳ ለጓዳ ሲያራውጠው ይገኛል።...." ዲባቶ መስፍን።

ዲባቶ መስፍንን፣ 'ሚጠት' ወይም Return/Homecoming/Restorationን *(ይህን እና ይህን ብቻ)* በተመለከተ መሳደብ ቀርቶ፣ ለመተቸት ብእር ማንሳት፣ እኔ "ቅን ህሊና ማጣት ነው" ከማለት በላይ ነው የምወስደው። ልሳንሲኛ (Linguist) ባልሆንም፣ የዲባቶ መስፍን ስራ የልሳንሲንን 'ሎጂክ' እና ህግ የተከተለ ለመሆኑ በድፍረት መመስከር የሚያስችል እውቀት አላጣም።

አዲስ አማርኛ ቃል ለፈጠረላቸው፣ ለምሳሌ በአስራ አራት *[ለልሳንሲን ባለሙያዎች፣ በቃላቱ መሃል ያለችውም አንዷት character space ከቦታ፣ ጊዜ፣ ጉልበትና ገንዘብ አኳያ ፋይዳ አላት]* ፊደላት የተገነባውን "አባቶቻችንና እናቶቻችን" የሚለውን፣ በ"አብናቶቻችን" ሲለውጠው፣ በሰባት ፊደላት የመቀነሱ ስኬት አይታየን። ደህና። "አብናቶች" ያለበትን ምክንያት፣ ሁሌም የ"እናት አገር" የምንል በመሆናችን፣ የአባትንም ድርሻ ለማከል ያደረገው የመሆኑን ሎጂክ ስናነብ፣ ይህን የፈጠራ ስራ የሚያደንቅ ህሊና እንዴት እናጣለን?

የዲባቶ መስፍንን ስራ እኔ የማየው፣ ከልሳንሲን ስራም በላይ ነው። ለምሳሌ ‘ክርስቲያን’ የሚለው ቃል፣ ግሪክኛ ነው። በኢትዮጵያዊ ቋንቋ ‘ደቀሄር’፣ “‘እስላም’ የሚለውም ቃል አረብኛ ነው፣ በ‘ኢትዮጵያዊኛ’ ቋንቋ ‘ሙሄፍና’ ተብሎ ሊጠራ ይገባዋል” ሲል፣ ኢትዮጵያዊያን ክርስቲያኖች፣ ሙስሊሞች ሊደግፉት ይገባቸው ይመስለኛል። ብሄራዊ አንድነታችንና ኢትዮጵያዊ ማንነታችን እንዲህ በዘር ፖለቲካ፣ በሃይማኖትም እየተገዘገዘ ባለበት ዘመን፣ ከተለያዩ ያገር ውስጥ ቋንቋዎች ቃላትን መፍጠሩም፣ ብሄራዊ ህዳሴን (በርቀትም ቢሆን) ያመጣ ይመስለኛል። ለዚህ ደግሞ፣ የባለሙያውን መስፍን ፈጠራ እያደነቁ፣ ነገር ግን የጎደለም ካለ ሙያዊ ሃሳብና አስተያየት እየለገሱ፣ ስራው ታላቅ አገራዊ ራእይ ያነገበ ነውና፣ ያንድ ሰው ብቻ ጥረት ከሚሆን፣ የ‘ሚጠት’ (Return/Homecoming/Restoration)ን አስፈላጊነትን የሚደግፉና በዚሁ ዙሪያ የዳበረ እውቀትና ልምድ ያላቸው ምሁሮቻችንና ሌሎችም በስርአተ-ትምህርትና ቋንቋ አካባቢ የሰሩና ለመስራት ፍላጎቱ ያላቸው ሁሉ ጋር በመተባበር ቢሰራ፣ ታላቅ ውጤት የሚያመጣ ውጥን ይመስለኛል።

አረቦች በሰብ-ሰሃራን አፍሪካ፣ የሙሄፍና (እስልምና) ሃይማኖትን በማስፋፋት ስም፣ (ግዛታዊ እና ኢኮኖሚያዊ...) ጥቅማቸውን ለማስፋት በርትተው እየሰሩ ያሉ መሆናቸውን ዲባቶ መስፍን ባለፉት ጽሁፎቹ ውስጥ፣ *[“ሰገላዊ አማረኛ (አማሮምኛ)” በሚል ርእስ እና፣ ‘መውደቅ የመነሳት ጅማሬ ነው’ በሚል ጥቅስ በታጀበው፣ የመጀመሪያ አካባቢ ጽሁፉ ውስጥ፣ ገጽ 5፣ 6 እና 7 ላይ ያሰፈረውን አብይና ዋና መልእክቱን እንዲያነብ አንባቢን እያስታወስኩ]* በዳርፉር የአፍሪካ ጥቁር ጎረቤቶቻችንና፣ ሙሉ በሙሉ የሙሄፍና (እስልምና) ሃይማኖት ተከታይ የሆኑ ውንድሞቻችን ላይ እያደረሱት ያለውን ግፍና በደል ጠቅሶ፣ አጀንዳቸው ሙሄፍናን (እስልምናን) ከማስፋፋት ባሻገር መሆኑን ያሳየበትን ጽሁፍ አንብቤያለሁ። አባይን ከምንጩ፣ ቀይባህርን ካናቱ ጀምሮ ለመቆጣጠር ለብዙ አሰርት አመታት ሲስሩ የኖሩት አረቦች፣ የመጨረሻው መጀመሪያ የሆነውን፣ ትንሿንና ደካማዋን፣ ግን ደግሞ ቀሪውን ኢትዮጵያ ለማበጥ የማይሳናትን ኤርትራን የመፍጠሩን ስራ አጠናቀዋል፣ የቀረውን ደግሞ ተያይዘውታል። (ከጥቂት ጊዜያት በፊት፣ አንድ የማውቀው ሙስሊም የአ.አ.ዩ. ተማሪ ጓደኛየ “ኢራን አገር ስኮላርሽፕ አግኝቼአለሁ። ወደ አካዳሚክ ኮርሶች ከመግባቴ በፊት ግን ሁለት አመት የእስልምና ሃይማኖት *[አሁን ዘነጋሁት እንጂ፣ የጠራልኝ የሃይማኖቱ ‘ፋክሽን’ ነበር]* መማር ግዴታ አለብኝ። ምን ትመክረኛለህ...” ያለኝ ነገር ትዝ ያለኝ፣ ዲባቶ መስፍን አርቦች በዳርፉራዊያን ሙስሊም ውንድሞቻችን ላይ ያደረሱትን ጭፍጨፋ ካስነበበኝ በኋላ ነበር)። ዛሬም ይህን ውስብስብና ከፊት ለፊታችን የተጋረጠውን አደጋ በሚገባ ለማወቅ *(መቼስ ለሁሉም የፈረንጅ ነብይ/ነጋሪ ታላስገባን አይሆንልን አይደል፣ በኛው ሰው የተጻፈውንማ መች ቁብ ስንለው?)* ይህን http://www.ethiomedia.com/absolute/3794.html ማንበብ ይጠቅማል።

በነገራችን ላይ፣ አብዛኛዎቹ የ“እስልምና ሀይማኖት” ስሞች የሚመስሉን ሰሞች፣ የአረብኛ ቋንቋ ቃላት እንጂ ከሃይማኖቱ ጋር ምንም ትሥሥር የላቸውም። ለምሳሌ ‘ሁሴን’ እና ‘ሃቢብ’ ማለት፣ ‘መልካሙ’ እና ‘ተወዳጅ/ወዳጆ’ “respectively” እንደ ማለት ናቸው። “አብዱል ባሪ” ደግሞ “ገብረ-እግዚአብሄር” እንደማለት ነው። ሸህ ገ/እግዚያሄር” ወይም “መምሬ አብዱል ባሪ” በሚሉ ስሞች መገረም ማቆም ያለብን ይመስለኛል። ለዚህ፣ “እስላም” የሚለው ቃል፣ እንዲሁ አረብኛ ቃል መሆኑንና፣ በራሳችን ቋንቋ ‘ሙሄፍና” ብንለው፣ በሃይማኖቶቹ መሃል ያለውን የልዩነት ክፍተት ለማስፋት የሚደክሙትን፣ ትንሽም ቢሆን ያጠብብባቸው ይመስለኛል።

**ሰዶ ከማሳደድ (ያለንን ጥለን የሌላውን ከማንሳት) እንድንም ይመስለኛል። (http://www.names4muslims.com/muslim-names/all/h-1.html) ይህን እንዳውቅ ላደረገኝ ዲባቶ መስፍን ምስጋናየ ይድረሰው።**

**ተማሪ ፍስሃ ከጠቀሳቸው አንዱ "ወሌ ነጋ"ን፣ በ'ዋዜማ' ድረ-ገጽ ላይ ያልጠበቅሁትን 'ረሶርስ' (የከዳነ ወልድ ክፍሌን መ/ቃላት) አገኘሁ። ወሌ ነጋን ለጥረታቸው፣ ለሙያዊ ቅንኣታቸው ሳመሰግናቸው ከታላቅ አድናቆት ጋር ነው።**

**የአማርኛ እና/ወይም ግእዝ ቃላቱን ግስ፣ ዘር እና ሚያ[4] ('ሙያ') በሚል የሰንጠርዥ ርእስ ስር ጥቂቶቹን አስፍሬያለሁ። መቸስ ሁሉንም ቃላት አንድ ባንድ ለማብራራት ጊዜው ብቻ ሳይሆን፣ ችሎታውም የለኝምና አንዳንዶቹን፣ [ዲባቶ መስፍንና ወሌ ነጋ፣ ሁለቱም የሰሩባቸውን ቃላት እያነጻጸርኩ ለማሳየት እሞክራለሁ።**

| ግስ | ዘር | ሚያ (ሙያ?) | English |
|---|---|---|---|
| አገባብ | | | |
| እለቄጥሩ | (ግ.፥ቅጥራን) | ረቂቅ፡ተፈጥሯዊ፡የብርሃን፡ኀይል፡ ሕዋስ። | electron |
| እለቄጥሩኛ | (ቅጥራን) | የእለቄጥሩ፡ጥናትና፡ሚያ፡መስክ። | electronics |
| እለቄጥሯዊ፡ጦማር | | እለቄጥሯዊ፡መልእክት፡መላላኪያ፡ዘዴ። | e-mail |

**እንደሚገባኝ ከሆነ፣ የe-mail' እኩያ አማርኛ '*እለቄጥሯዊ ጦማር*' መሆኑ ይመስለኛል። 'እለቄጥሩ' *[(electron) የሚለውን እንግሊዘኛ፣ ወዳማርኛ ለማልመድ ይመስላል (philosophy ብሎ 'ፍልስፍና' እንደሚለው]* የሚለው ግስ፣ ዘሩ (ቅጥራን) መሆኑ ነው የተገለጸው (http://gzamargna.net/html/ga_merbebiya_2002_yesletgs1.html።**

**እናም ከ 'ጦማር/mail' ጋር አጣምሮ "electronics mail/e-mail" እንዲሆን ነው። 1ኛ) በመዝገበ ቃላቱ ፍቺ መሰረት፣'ቅጥራን' ን ከelectronics.(አሌክትሪክ) ጋር የሚያመሳስለው ቀርቶ፣ በዙሪያ ጥምጥምም ቢሆን electronicsን የሚገልጽ ፍቺ ቀርቶ ድምጸትም ያለው አንድም ቃል የለም። 2ኛ) አንድ ቃል፣ ቃሉ ከሚወክለው ነገር ጋር የሚያገናኘው ምንም ነገር የለም**

[4] *'ሙያ' 'ሚያ' ከሚለው ቃል የመጣ ይመስላል፤ ውሎዉን በሞላ ሲሰሩት እንደሚውሉት ስራ/ሙያ እንደማለት። የገበሬ ውሎዉ (ሲሰራ የሚውለው፣ ሚያው/መዋያው) እርሻ ላይ ነው፤ እናም የገበሬ ሙያ (ሚያ) እርሻ ነው' እንዲሉ። እንዲህ ሃብታም ግእዝ/አማርኛ እያለልን.... ።*

*(ዲባቶ መስፍን ይህን በሚገባ ገልጾታል)*፤ እና በስምምነት ‘ይሁን’ ብለን ቃሉን እንውሰድ ቢባል እንኳን፣ ‘እለቄጥሯዊ፡ጦማር’ የሚረባ (እርባታ) ግስ አይመስልም።

እንግዲህ በአማርኛ He emailed me. እና ‘I am emailing him’ ብለን መጻፍ ቢኖርብኝ፡-

“(እሱ)እለቄጥሯዊ፡ጦማር ጻፈልኝ” *ወይም በጣም የተሻለ የሚመስለውን* “(እሱ) እለቄጥሯዊ ጦማር ላከልኝ” ነው ልንለው የምችለው የሚመስለኝ።

‘I am emailing him’ ለሚለው እንግሊዝኛ ደግሞ አንባቢ የራሱን የተሻለ አማርኛ ትርጉም ይስራና፣ ይኸንን እና የዲባቶ መስፍን የ ‘email’ እኩያ በሆነው በ“ጾዳቤ *[ወላይትኛውና አማርኛው ‘መብራት እና electric፣ ባንድነት ሲሆን ደግሞ (electronics mail)’ የሆነው፣ ከወላይትኛው ‘ጾፓስ’ እና ከአማርኛ እና እንግሊዝኛው ‘ደብዳቤ’ እና ‘mail’]* በመጠቀም የራሱን አረፍተ ነገር ሰርቶ ቢያወዳድር የትኛው የተሻለ እንደሆነ ለመፍረድ ይቻል ይመስለኛል።

ተማሪ ፍስሃ ባለፈው ጽሁፉ መግቢያ ላይ ወ’ዳሰፈረው ጉዳይ ልግባ። እንደሚመስለኝ፣ የፍስሃ አጀንዳ፣ ልሳንሲን (linguistics) ሳይሆን፣ ዲባቶ መስፍንም እንዳለው፣ በ“ሰበካ ሽወዳ” ይመስላል። የአንባቢን ትኩረት በሚስብ፡- “*ለካ መሰገሉ* (ሰገለኛው) *ገናኝ* (‘potential’) *የሃይማኖት መሪ ኖሯልና። ገናኝ የሃይማኖት ደቀ-መዝሙርም አፍርቷል*” በሚል አማርኛ ጀምሮ፣ ትንሽ ትንሽ እውነት ይዞ፣ የነገሮችን ቅደም ተከተል በመጠበቅ፣ ያልተባለ *(በማስረጃ ሊደገፍ የማይችል ሃሳብን)* እንደተባለ በመደርደር አንባቢን ለማሳመን ያለው ችሎታ… በዚህ መቸም የአጻጻፍ ችሎታውን (ቃላት አመራረጥ፣ ‘አብዛኛውን ሃሳቤን ይደግፉልኛል’ ያላቸውን ምሁራን ስምና ስራዎቻቸውን ግርጌ ማስታወሻ ላይ ማስፈርን *[ዋናውን ጽሁፍም ለማንበብም ጊዜው ይቸግራልና። ለነገሩ ዋናውም፣ ግርጌ ማስታውሻውም ውስጥ፣ የትኛው ገጽ ላይ? ማን? ምን አለ?..አንድ የተጠቀሰ የለም]*… ላይ ምን መግባት እንዳለበት… ወዘተ ችሎታውን ሳላደንቅ ባልፍ ፍትህ የሰጠሁ አይመስለኝም[5]።

“*ለካ መሰገሉ* (ሰገለኛው) *ገናኝ* (‘potential’) *የሃይማኖት መሪ ኖሯልና። ገናኝ የሃይማኖት ደቀ-መዝሙርም አፍርቷል*” በሚለው መግቢያ፣ 1ኛ) ይህ ክርክር ስለ ልሳንስን (linguitics) ሆኖ እያለ ለምን ዘሎ ሃይማኖት ውስጥ እንደገባ አይገባኝም። 2ኛ) ድምጸቱ (tone)ኑ፣ የትችቱን ሙያዊ አለመሆን ከማሳየት በቀር ምንም አይናገርም። ምክንያቱም፣ ገናኝ የሃይማኖት መሪ ወይም ደቀ-መዝሙር ነኝ/ነው’ ያለ የለም። ሙያዊ ሂስ/ትችት እንዲህ አይደለም። ቅኔ አይሉት አሽሙር ይህ አይነት አመጣጥ ከገንቢነቱ ይልቅ አፍራሽነቱ ያመዝናል። ሀይማኖትን ሰው የማይሰራው ግን ደግሞ አይምሰለን። ከአምስትና ስድስት አሰርቶች ያልበለጠ እድሜ ያለው “ሳይንቶሎጂ” ‘ሮን ሃባርድ’ የሚባል አሜሪካዊ የሰራው ሃይማኖት ነው (http://en.wikipedia.org/wiki/Scientology)።

---

[5] በዚህ ችሎታው ውስጥ የታየኝ ነገር ቢኖር፣ ከጥንት ጀምሮ ታላቅ ራእይ ይዘው የተነሱት-- የፈላስፋው ዘርአ ያእቆብ፣ አጼ ቴዎድሮስ … ራእይ፣ በስመ-ሃይማኖት፣ በ’ሰበካ ሽወዳ’ እንዴት እንደመከነባቸው ነው። በ“ሃይማኖት” ላይ ተንጠልጥሎ፣ አዲስ ሃሳብ ይዞ የተነሳን ሰው “መኮርኮም” ከጥንት ጀምሮ ያለ በሽታችን፣ ዛሬም ያልለቀቀን በሽታ መሆኑ ነው የታየኝ።

"እግዜር ሰውን አልፈጠረውም፣ ሰው ነው በአምሳሉ እግዜሩን የፈጠረው" ብለው የጻፉ በርካታ ፈላስፎች፣ ያገር ሰዎችም ጭምር፣ መኖራቸውንም እንስተው አይመስለኝም። ታላቁ ጸሃፊ ዶ/ር ከበደ ሚካኤልም፡-

ጽድቅና ኩነኔ ቢኖርም ባይኖርም
ከክፋት ደግነት ሳይሻል አይቀርም፤

ብለው ሲጽፉ፣ አይምሮዋቸው ውስጥ ብልጭ ብሎ የሄደውን ሃሳብ ላምሰለሰለው፣ ታላቅ ፍልስፍና ነው። እኔን ይህ ያስደምመኛል። ኧረ ያቺ ያልተማሩት ያያ ከልክሌ[6] ሚስትም ይፈላሰማሉ። እንዲህ ሆነ፦

በስንት ጸሎትና ስእለት የደረሰ አንድየ (እንዲያው አንድ) ልጃቸውን ሊድሩ፣ ጠጁ እየተጠመቀ፣ ጠላው እየተጣለ፣ እየተዘፈነ፣ ሰርጉ እየተሰረገ፣ ያያ ከልክሌ ሚስት ጉድ ጉድ እያሉ 'እንዲያው አንድ ሁለት ልጅ ጨምሮ ቢለግሰኝ እስቲ አሁን...' እያሉ እያሰቡ፣ እንዲያው ዘጠኝም ስምንትም ልጅ ወልደው በዳሩና የልጅ ልጅ ባዩ ጎረቤቶቻቸው እድል እየቀኑ፣ መልሰው ደግሞ 'ይሁን እስቲ! እሱኑ ይባርክልኝ። ወልዶ ከብዶ ልጅ በልጅ ያደርገኛል' ያሉት ልጃቸው፣ ሊዳር ቀናት የቀረው አንድየ ልጃቸው፣ በድንገተኛ ህመም ሞተ። ያያ ከልክሌ ሚስት፣ ቀብር ላይ አስለቃሹን ጠርተው እንዲህ አሉት አሉ፦

"ዘጠኝ ታድናለህ፣ አንድ ትገድላለህ፣
የሴት ልጅ ነህና ምን ፍርድ ታውቃለህ" (ገጽ 100፣ unheard voices፣ ዲባቶ (ዶ/ር) ፈቃደ አዘዘ)።

&&&&&&&&&&&&&&&&&&

*"... ይህን የመሰለ ጸሎት አደርግ ነበረ። አንድ ቀን እኔ ወደ ማን ነው የምጸልየው አልኩ። በእውነት የሚሰማኝ እግዚአብሄር አለን? በዚህም አሳብ በጣም አዝኜ እንዲህ አልኩ። ዳዊት እንዳለ እንዴት ምንኛ ልቤን በከንቱ አጸደኳት። ኋላም አሰብኩ። ይህ ዳዊት እንዲህ የሚለው ጆሮን የተከለ አይሰማምን? በእውነት እንድሰማበት ጆሮ የሰጠኝ ማን ነው? ... ወደዚህስ አለም እኔ እንደምን መጣሁ? ከወዴትስ መጣሁ? ከአለም በፊት ብኖር የህይወቴ መጀመሪያና የእውቀቴ መጀመሪያን ባወኩ። እኔ በገዛ እጄ ተፈጠርኩን? ነገር ግን እኔ በተፈጠርኩ ጊዜ አልኖርኩም። አባት እናቴ ፈጠሩኝ ብልም እንድገና ወላጆችና የወላጆችን ወላጅ፣ ወላጅ የሌላቸውን በሌላ መንገድ ወደዚህ አለም የመጡትን እንደኛ ያልተወለዱትን የፊተኞቹ ድረስ ፈጣሪያቸውን እፈልጋለሁ። እነርሱም በወለዱ የፈጠራቸው አንድ ህላዌ አለ ከማለት በቀር የጥንት መወለጃቸውን አላውቅም።..."*

*(መጽሃፈ ፍልስፍና ዘርዓ ያዕቆብ፣ ገጽ 10-11)።*

ባይልልን ነው እንጂ፣ እኚህ ፈላስፎቻችን (የጥንቶቹም ሆኑ ያሁኖቹ) የተናገሩዋቸውን/የጻፉዋቸውን/የተነተኗቸውን፣ በዚያ ሁሉ የተለያየ ቋንቋ፣ ባህልና፣ ልማድ እና አስተሳሰቦች ውስጥ ያለንን ሃብት ብንመረምር፣ 'አርስጣጣጣሊስ' 'ኤንግልስ' ስንል፣ የፈረንጅ ነብይ ስንጠቅስ ባልተገኘን ነበር (*የጎደሉንን፣ ግን ደግሞ ጠቃሚ የሆኑትን፣ ከሌሎቹ የመውሰድ አስፈላጊነት እንዳለ ሆኖ*)።

---

[6] አያ ከልክሌ፣ እኔ የፈጠርኩት ባህሪ ነው። ስነ-ቃሎቹ ግን ያሉ፣ (የታተሙም/ያልታተሙም) ሊሆኑ ይችላሉ።

በድጋሜ ግልጽ ለማድረግ፡- እኔ የማናቸውም አብሄር-ነክ (god-related) ሃይማኖት ተከታይ አይደለሁም። የኔ ሃይማኖት በ'ምክነታ' (reasoning) መኖር ነው። ይህ እንደ ግለ-ሰብ፣ የኔ የራሴ ምርጫ ነው። ይህን ሃይማኖቴን ለማስተላለፍም በርትቼ እሰራለሁ--ሌላው እንደሚሰራው ሁሉ። በቅርቡም "እግዜር (አብሄር) ተፈተነ" በሚል ርእስ የሚታተመውን መጽሃፌን አሰራጫለሁ። እንደ ኢትዮጵያዊ ዜጋ ደግሞ ሁላችንም በምንጋራቸው፣ ለምሳሌ እንደ ያገር አስተዳደር፣ ብሄራዊ የስራ ቋንቋ... እንዲህ የዲባቶ መስፍን ስራዎች... ወዘተ በመሳሰሉት ጉዳዮች ላይ፣ የሃገሪቱ ዜጎች ሁላችንም ልንወያይበት፣ ልንሳተፍበት የሚገባ ይመስለኛል። ባጭሩ "ሀይማኖት የግል ነው፣ አገር የጋራ ነው"።

**&&&&&&&&&&&&&&&&&&&&&&**

ሌላው "ዘለፋማ ዘለፋ ነው። በሌላ ሳይሆን 'ነቀፌታ' በሚለው የቃሉ ስሜት ነው" ለሚለው፣ መቸስ 'ዘለፋ' እና "ነቀፌታ" ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ለመሆኑ የሚጠቀስልን መ/ቃላት ያለ አይመስለኝም። የ'ዘለፋ' ን እና 'ነቀፌታ'ን ፍቺ (አንድነትና ልዩነት) እናጣውም አይመስለኝም። ይቺን ይቺን የቋንቋ 'ጫወታ' በጣም እንደምትጫውታት የ'ሰገል' ፍቺ አደራደርህ ላይም አይቻለሁ። 'ሰገል' ማለት "ጥንቆላ፣ እውቀት" ነው *(ደስታ ተክለ ወልድ መ/ቃላት፣ ገጽ 1122)*። አለቀ። 'ሰገል' እና 'እውቀት'ን በፍቺ ለማራራቅ ስለፈለግህ ብቻ *"'ሰገል' መላን፣ ግምትን፣ ጥበብን፣ እውቀትን የሚያሰማ መሆኑ ባይካድም... "* ትለንና፤ 'ጥንቆላ'ን ለማስጮህ ስለፈለግህ ደግሞ፣ "'<u>መደበኛ</u> ፍቺው... '" የሚል፣ *[መ/ቃላቱ ውስጥ የሌለ]* አጽንኦት *[መስመሩም የለም]* አስከትለህ "ጥንቆላ፣ ሟርት ነው" አልከን። በተጨማሪም "ሰገለኛ ማለት 'ጠንቋይ'፣ 'ሟርተኛ' ማለት ነው" ነው ያልከን *('ሰገል' ከሚለው ቃል ፍቺ ስር 'ሟርት፣ ሟርተኛ' የሚል ጨርሶ የለም*[7] *። የ'ጥንቆላ' እና 'ሟርት' ፍቺ ተመሳሳይነታቸው ደግሞ በጣም ሩቅ ነው—የት የለሌ! 'ጠንቋይ' በደቀሄርፍና [በክርስትና] እምነት ለደብተራ፣ በሙሄፍና (እስልምና) ደግሞ ለቃልቻ የሚሰጥ፣ እንደየሃይማኖቶቹ፣ በሃይማኖቱም ትምህርት በዙ ያወቁ፣ የመጠቁ፣ ትንቢትም እጣ ፈንታም፣ የወደፊቱን ሁሉ ማሳወቅ ለሚችሉ፣ ያፍዝ ያደንግዝና ሌላም አስማት፣ መተት፣ ወዘተ... ለሚያውቁ (እኔ እንኳን አላምንም)፥ እንዲያውም የ'ጠንቋይ' ሌላው እኩያ ስም 'አዋቂ' ነው። 'ሟርተኛ' ደ'ሞ ምንም አይነት የሃይማኖት ትምህርትና እውቀት ለሌለው ሰው ሁሉ የሚሰጥ ነው።*

ያ አያ ከልክሌ፣ እንዲህ ሰው አጉልኛ ብልጥ ሲሆንበት "ይቺን ለኛ፣ ጥሬን ለደገኛ" ይላል። እንዲያው 'ድከም ቢለኝ' ነው'ይ፤ ለነገር ለነገሩ... ይቺን ይቺን ... የ'ሟርት'ን እና 'ጥንቆላ'ን ፍቺ፣ ልዩነትና አንድነት፣ ታንተ በላይ የማውቅ አይመስለኝምና፣... የኔው እሰጥ አገባ እንዲያው ጉንጭ ማልፋት ነው።

**&&&&&&&&&&&&&&&&&**

"...ይህ በቅዱሳት መጻህፍት የተጻፈ ሁሉ እውነት ይሆን? ብዬ አሰብኩ። በጣም አላወኩምና የተማሩና ተመራማሪ ሰዎችህ እውነትን እንዲነግሩኝ ሄጄ ልጠይቃቸው ብዬ ብዙ አስብኩ። ... በየልቦናቸው ያለውን ካልሆነ በቀር ሌላ ምን ይመልሱልኛል ብዬ አሰብኩ። ሰው ሁሉ የኔ

---

[7] *ያንተ መ/ቃላት ሌላ ሊሆን እንደሚችልም እያሰብኩና፣ 'ሟርት'ን ያመጣሃው ከዚያ ሊሆን እንደሚችልም እገምታለሁ። እንዲህ ሲሆን ግን ምንጩን መጥቀስ ያስፈልጋል። ሙያዊ ሂስ [ትችት] አቀራረቡ እንዲያ ነው።*

**ሃይማኖት እውነተኛ ናት ይላል። በሌላ ሃይማኖት የሚያምኑ ሃሰተኞች የእግዚአብሄር ጠላቶች ናቸው። ዛሬም ቢሆን ፈረንጆች ሃይማኖታችን መልካም ናት፣ ሃይማኖታችሁ ግን መጥፎ ናት ይሉናል። እኛም መልሰን እንደዚያ አይደለም የናንተ ሃይማኖት ናት መጥፎ፣ የኛ ሃይማኖት ግን መልካም ናት እንላቸዋለን። … ስለ ብዙ ሃይማኖቶች ጉዳይ አንድ የፈረንጅ መምህር ጠየኩ። እሱ ግን ሁሉን እንደ ራሱ ሃይማኖት ፈታው። ኋላም አንድ ትልቅ የኢትዮጵያ መምህር ጠይኩ። እርሱም ሁሉንም እንደ ሃይማኖቱ አድርጎ ተረጎመው። እስልምናን አይሁድንም ብንጠይቅ እንዲሁ እንደ ሃይማኖታቸው ይተረጉማሉ። ታድያ እውነት የሚፈርድ የት አገኛለሁ? የኔ ሃይማኖት ለእኔ እንደሚመስለኝ እንዲሁ ለሌላውም ሃይማኖቱ እውነት ይመስለዋል። ነገር ግን ጽድቅ አንዲት ናት።… "**

*(ዳንኤል ወርቁ፣ መጽሃፈ ፍልስፍና ዘርዓ ያዕቆብ፣ ገጽ 12-13)።*

**&&&&&&&&&&&&&&&&&&&&&&**

**"ጽድቅና ኩነኔ ቢኖርም ባይኖርም፣
ከክፋት ደግነት ሳይሻል አይቀርም፣ "**
*ከበደ ሚካኤል፥*

**ተፈጠመ!**

Gelanew-kirar@hotmail.com